የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስረኛ ዓመት ቁጥር 35
ሠመራ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት
ጠባቂነት የወጣ

10th year No.35
Semera 7th July, 2006

ማውጫ

የወረዳ አስፈፃሚ አካላትን ለማደራጀት እና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 35/1998 ዓ.ም

የወረዳ አስፈፃሚ አካላትን ለማደራጀት እና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

መግቢያ

የተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት ራስን በራስ ማስተዳደር መርህ በመከተል እያንዳንዱ የወረዳ መስተዳደር አካባቢውን የማልማትና በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት እቅዶችን የማዘጋጀትና የማውጣት በውስጣዊ ጉዳዩቹ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት የሰጠው መሆኑን ስለሚደነገግ

በዚሁ መሠረት የወረዳው አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባራቸውን ለይቶ በማስቀመጥ ግልጽ ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለለማድረግ እና በድህነት ቅነሳና በገጠር ልመማት ያነጣጠረውን የክልሉን ስትራቴጂክ እቅድ ከግብ ለማድረስ የተሻለ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

የአፋር ብ/ክ መንግስት በተሸሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

ክፍል አንድ

አጠቃላይ ድንጋጌ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹የወረዳ አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 35/1998 ››ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

1. ‹‹ህገ መንግስት›› ማለት የ 1994 የተሻሻለው የክልል ህገ መንግስት ነው
2. ‹‹የክልል መስተዳድር ም/ቤት›› ማለት የክልሉን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ስ/ተግ/ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 30/98 /የተሻሻለው/ የተቋቋመው የክልሉ አስፈፃሚ አካላት /የካቢኔ /ም/ቤት ነው።
3. ‹‹ወረዳ››ማለት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 73 ድንጋጌ ስር የተመለከተውንና ባልተጣከለ አስተዳደር ራሱን ለማስተዳደር ከክልል በታች የተቋቋመ የአስተዳደር እርከን ነው።
4. ‹‹ምክር ቤት ›› ማለት የወረዳ ም/ቤት ማለት ነው።
5. ‹‹መስተዳድር ምክር ቤት ›› ማለት የወረዳው አስፈፃሚ አካላት ም/ቤት ማለት ነው።
6. ‹‹ካቢኔ›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር የተዘረዘሩት ጽ/ቤቶች ማለት ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ ወረዳ መስተገዳደር ም/ቤት መቋቋም

አንቀጽ 3

ስለ ወረዳ መስተዳደር ም/ቤት አደረጃጀት

1. በተሸሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 82/2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ መስተዳደር ም/ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል።

   ሀ/ የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ

   ለ/ የወረዳ ም/አስተዳደሪ

   ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር የተዘረዘሩ የጽ/ቤት ኃላፊዎች

   1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሐ የተመለከተው የጽ/ቤት ኃላፊ በመስተዳደር ም/ቤት ስብሰባ ላይ መገኘት ካልቻለ ምክትሉ የሚወከልው በአባልነት ይሳተፋል።

አንቀጽ 4

ስለ ወረዳ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር

የወረዳ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 83 ድንጋጌ ስር የተመለከተው እንነደተጠበቀ ሆኖ በዚህ የሚከተሉት ዋና ዋና ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ይጠበቃል የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል ስራቸውን ያስተባብራል፤
2. የፌደራሉና የክልሉ መንግስታት ፖሊሲዎች ህጎች እቅዶችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በስራ ላይ እዲውሉ ያደርጋል፤
3. በወረዳው ያሉ አርብቶ አደሮችን የኑሮ እንቅስቃሴ ይከታተላል በእንስሳት ሀብት በግጦሽ ልማት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች
4. ላይ ከሚመለለከታቸው አካለት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
5. በህግ መሠረት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ገቢዎችን ይሰባሰባል ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳ ም/ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፤
6. ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ አስተዳደራዊ እና የበጀት እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል ። በተግባር ላይ እንዲውሉም ያደርጋል፤

አንቀጽ 5

ስለ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህግ መንግስት አንቀጽ 85 ድንገጋጌ ስር የተመለከተው ይሆናል።

አንቀጽ 6

ስለ ወረዳ ምክትል አስተዳደር ስልጣንና ተግባር

የወረዳ ም/አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህግ መንግስት አንቀጽ 86 ድንጋጌ ስር ተመለከተው ይሆናል።

አንቀጽ 7

ስለ ወረዳ ጽህፈት ቤቶች መቋቋም

የሚከተሉት የወረዳ ጽህፈት ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።

1. የአርብቶ አደር ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት
2. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት
3. የፀጥታና አስተዳደር ጉዳዮች ጽ/ቤት
4. የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት
5. የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት
6. የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት
7. የትምህርት ጽ/ቤት
8. የማስታወቂያና ህዝብ አደረጃጀት ጽ/ቤት
9. የውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት
10. የኤች ኤይ ቪ ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት

አንቀጽ 8

ስለ ወረዳ ጽህፈት ቤቶች የጋራ ስልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ የወረዳ ጽህፈት ቤት፦

1. የጽህፈት ቤቱን ስትራቴጅክ እቅድ ያዘጋጃል ሲፀድቅ ይፈጽማል አፈፃፀሙንም ይከታተላል ፤
2. የጽህፍት ቤቱን ዓመታዊ በጀት ለወረዳ መስ/ም/ቤት ያቀርባል በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ በፋይናንስ ህግ መሠረት ስራ ላይ ያውላል፤
3. በክልሉ ሠርቪስ ህግ መሰረት ሠራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል ያሰናብታል፤
4. ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የክልሉን አዋጆች ደንቦች መመሪያዎችንና ፖሊሲዎችን ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ያረጋግጣል፤

አንቀጽ 9

ስለ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በጠቅላላው

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ና /ሐ/ መሠረት የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪና የካቢኔ አባላት የሆኑ የጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለወረዳው አስተዳዳሪ እና ለመስተዳድር ም/ቤቱ ይሆናል።

2. የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች በብቃታቸውና ፖለቲካ አመራራቸው በም/ቤቱ አብላጫ ድምፅ የተደገፉ መሆን አለባቸው፣
3. ለየጽ/ቤቱ ኃላፊዎች የሚመሩትን ጽ/ቤቶች ይወክላሉ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላሉ፣
4. የጽ/ቤቶቹ ሰበተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋሉ የጽ/ቤቱን ውጤታማ የስራ አመራር ስርዓት ይዘረጋሉ ስለተግባራዊነቱም ይቆጣጠራሉ፣
5. የጽ/ቤት ኃላፊዎቹ እንደመስተዳድር ም/ቤት /ካቢኔ/ አካል ለሚወሰኗቸው ውሳኔዎች የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አላቸው።

ክፍል ሶስት

የጽ/ቤቶች ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት

አንቀጽ 10

የአርብቶ አደር ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተለው ዝርዝር ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. በክልሉ የሚወጡትን የአርብቶ አደሩን የእንስሳት ሃብት ልማት እና ሌሎች የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲዎችንና ህጎችን በወረዳው ሰውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ህችን በወረዳው ውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። ተፈፃሚ ስለመሆናቸውም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
2. በወረዳው በእርሻ ስራ ለተሰማሩ አርብቶ አደሮች የግብርናና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ያቀርባል፣
3. መካከለኛ የእንስሳት ህክምና ማዕከላት እንዲቋቋሙና ሰርጭቱ እንዲያድግ ያደርጋል። ተፈፃሚ ስለመሆናቸውም ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣
4. በወረዳው የመስኖ ልማት ስራ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል ለዚሁ የሚጠቅም የአፈፃፀም ስልት ያዘጋጃል። ያስፈፅማል፣
5. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከወረዳው ካሉ ገጠር ቀበሌዎች የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ክትትል ያደርጋል፣
6. በእንስሳት ኃብት ልማት ላይ እና በሌሎች የግብርና ውጤቶች ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸውን ወቅታዊ ሁኔታዎች ይከታተላል ወረርሽኝና ተዛማጅ ተባዮችን ለመከላከል ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
7. በወረዳው የደን ሃብት ልማት እንዲስፋፉ ጥረት ያደርጋል የደን ተክል ችግኞች እንዲሰራጩና የቴክኒክ አገልግሎት እንዲደርስ ይጥራል፣

8. በወረዳው የሚደርሱ የእርዳታ እህልና ቁሳቁሶች በአግባቡ ይይዛል ይጠብቃል ለተጠቃሚዎች በአግባቡ መድረሱን ይከታተላል ይቆጣጠራል የአደጋ መከላከል ስራዎችን ይሰራል፣
9. የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን በሚመለከት የወረዳው አርብቶ አደር ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል። ስራውንም በበላይነት ይመራል። ይቆጣጠራል፣
10. በገጠር ልማት እንቅስቃሴ የገጠር ሴቶች የኢኮኖሚ አቅማቸው በሚያሳድግ ስራ እንዲሳተፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል የምክር አገልግሎት ይሰጣል ያበረታታል፣
11. በወረዳው የደን የዱር አራዊት እንዲሁም አጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት ልማትን በሚመለከት በበላይነት ይሰራል ይቆጣጠራል፣
12. በወረዳው የአካባቢ ጥበቃ ስራዎን በሚመለከት በበላይነት ይመራል ህብረተሰቡ በአካባቢ ጥበቃና መሬት አጠቃቀም ግንዛቤው ከፍ እንዲል ያደርጋል የተፈጥሮ ሃብት ውድመትን እንዲከላከሉ ያነሳሳል፣ ያደራጃል፣
13. የእንስሳትና እርሻ ልማቱን በገበያ እንዲመራና ገበያው የሚስፋፋበትን ዘዴ ይቀይሳል ተግባራዊ ያደርጋል፣
14. በወረዳው ኢንቨስተሮች የሚሰጥ የእርሻ መሬትን እያጠና ያዘጋጃል ከሚመለከተው የክልል አካል እያጠና ያዘጋጃል ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር በጋራ ይሰራል ባለሃብቶች ከአርብቶ አደሩ መሬት ሲከራዩም ህግ በሚፈቅደው መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣
15. በወረዳው የህብረት ስራ ማህበራት እንዲስፋፉ ያደርጋል ያደራጃል ይከታተላል፣
16. የወረዳ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ዴስክን እንዲሁም የህብረት ስራ ማህበራት ዴስክን በበላይነት ይመራል ስራቸውን ይቆጣጠራል ይከታተላል፣
17. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤትና እንደ ስራ ባህሪያቸው ለክልል አርብቶ አደር ግ/ገ/ል/ቢሮ እና ለአ/መ/ ምግብ ዋስትና ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ 11

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የክልሉን የፋይናንስ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች በወረዳው ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል አስፈፃሚ አካላቱ ህግጋቱን ተከታትለው መስራታቸውን ይቆጣጠራል። ይከታተላል።

2. የክልሉን የልማት ስትራቴጂ መሰረት ያደረገ የወረዳው የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት እቅድ በማዘጋጀት ለወረዳው መስተዳድር ም/ቤት /ካቢኔ/ ያቀርባል ሲፀድቅም አፈፃፀሙን ይከታተላል።
3. በወረዳው ውስጥ ካሉት የአስፈፃሚ ጽ/ቤቶች የሚቀርቡለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት ጥያቄ ያለፈውን ዓመት በጀት አፈፃፀም መርምሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ የወረዳ በጀት አዘጋጅቶ አስተያየቱን በመጨመር ለወረዳው መስተዳድር ም/ቤት /ካቢኔ/ ያቀርባል ሲፀድቅ አፈፃፀሙን ይከታተላል።
4. የወረዳው የገቢ ምንጮች ተብለው በህግ ተለይተው የተሰጡትን ቀለጥና ግብር በአግባቡ እንዲወሰኑ እንዲሰበሰቡ ሂሳቡም በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል። የተሰበሰቡ ገቢዎችን ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያሳውቃል። በተጨማሪም የገቢ ምንጮችንም ያጠናል ለሚመለከተው አካል ለውሳኔም እንዲቀርቡ ያደርጋል፣
5. በወረዳው የሂሳብ አያያዝ ስርዓት የፋይናንስ ህግና ደንብን ተከትለው መፈፀማቸውን ያረጋግጣል የሂሳብ ሰነዶችን ይመረምራል፣
6. የኢንስሊክሽን ሪፖርቱን ለዋና አስተዳዳሪውና ለክልሉ ፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፣
7. የወረዳው የገቢ ምንጭ ተብለው ተለይተው ከተሰጡት ውጭ ያሉ የገቢ ግብርና ቀረጥን በህጉ መሰረት ይሰበስባል ለክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ገቢ ያደርጋል፣
8. የወረዳውን የልማት አቅም ያጠናል፣ ጠቅላላ የልማት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣
9. በክልሉ መንግስት እንዲሰሩ ፈቃድ የተሰጣቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረሰናይ ሰብዓዊ ድርጅቶች የስራ እቅዳቸውን ከወረዳ የልማት ስራ እቅድ ጋር ያቀናጃል፣
10. የወረዳውን ንብረት ይቆጣጠራል ያስተዳድራል፣
11. በወረዳው ስነ-ህብዝን የተመለከቱ ጉዳዮች ይሰራል። በወረዳው የልማት እቅድ ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል።
12. በወረዳው የመረጃና ኢንፎርሜሽን ስርዓት በመዘርጋት የተጠናከረ የእቅድና የልማት ክንውን እንዲቀላጠፍ ያደርጋል፣
13. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት እና ለክልሉ የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያቀርባል፣

አንቀጽ **12**

የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተለው ዝርዝር ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የወረዳ ጽ/ቤቶች አቅም ግንባታን የሚመለከቱ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ይከታተላል።
2. የወረዳ ጽ/ቤቶች አቅም ግንባታን የሚመለከቱ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ይከታተላል።

3. ከክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ጋር በመተባበር ለወረዳ የስራ ኃፊዎችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል።
4. የወረዳውን የአቅም ግንባታ ፍላጎት ለመለየት የሚያስል ጥናቶች ያካሂዳል።
5. በወረዳው የሚካሄደውን የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በበላይነት ይመራል ያስተባብራል ያስፈፅማል።
6. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አፈፃፀም በተገልጋዮችና በጽ/ቤቶች ተገቢውን ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል።
7. የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲና መመሪያዎች በወረዳው ባሉ አስፈፃሚ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣
8. በወረዳው የሚቀጠሩ ሠራተኞች የአቀጣጠራቸው፣ አመዳደባቸውና የደረጃ እድገት አሰጣጣቸው በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ደንብናመመሪያ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል ይከታተላል፣
9. በወረዳው አስፈፃ አካላት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚታየውን የሰው ኃይል ልማት አስተዳደር ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሠራር ድክመቶችን ክትትል በማድረግ ተጠያቂነትንና ውጤታማነትን ሊያመጡ የሚያስችሉ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።
10. በወረዳው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣
11. ወቅታዊናመደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ፣/ቤት እና ለክልሉ የአቅም ግንባታ ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ **13**

የፅጥታና አስተዳደር ጉዳዮች ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በወረዳው ህግና ስርዓት መከበሩንና የሕብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣
2. በወረዳው ውስጥ በጎሳዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
3. በወረዳው መልካም አስተዳደር እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ለሚያጋጥሙ ችግሮ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል።
4. የወረዳው የሚሊሻእና የፖሊስ ጽ/ቤቶችን በበላይነት ይመራል ስራቸውን ይቆጣጠራል ይከታተላል።
5. የወረዳውን የሚሊሻ ሃይል ስልጠናና ምልመላን እንዲሁም ጥቅምና አስፈላጊ መገልገያዎችን በሚመለከት ከክልል የፍትህና አስተዳደር ቢሮና ከሚሊሻ ጽ/ቤት ጋር በመሆን በጋራ ይመራል ያስተባብራል፣
6. በህዝብ ፀጥታና ደህንነት ጉዳዮች ላይ አግባብነት ካላቸው የክልልና የአጎራባች ወረዳዎች መስሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት ይመሰርታል።

7. በወረዳው ውስጥ የሚነሱ አስተዳደራዊ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች ሲቀርቡለት ጉዳዮቹን ያጣራል ይፈታል ከአቅሙ በላይ ከሆነ ለወረዳው አስተዳዳሪ እና ለክልሉ የፍትህና አስተዳዳር ጉዳዮች ቢሮ ያቀርባል።
8. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት እና ለክልሉ የፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ 14

የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ጤና ጥበቃ በተመለከተ የሚወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች በወረዳው ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል ተፈፃ መሆናቸውንም ያረጋግጣል ይቆጣጠራል፣
2. ጤና ጥበቃናበሽታን ለመከላከል መሠረት ያደረገ የጤና አገልግሎት እንዲኖር ለወረዳው ህዝብና ቀበሌዎች ድጋፍ ይሰጣል ያስተባብራል ይመራል።
3. በወረዳው የጤና ኬላዎች ይገነባል። ያስተዳድራል።
4. ጤና ጣቢያዎችን ያስተዳድራል ይቆጣጠራል።
5. በወረዳው የሰነ ተዋልዶና የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል።
6. ጤና ነክ በሆኑ ጉዳዮች ለእናቶች ስለ ህፃት ክትባት፣ እንክብካቤና በመሳሰሉት ጉዳዮች የጤና ግንዛቤ እንዲያገኙ ትምህርት ይሰጣል።
7. ከክል ቴና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመተባበር በወረርሽኝ ደረጃ ሊነሱ የሚችሉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ዘዴዎች ያቅዳል ያስፈፅማል፣
8. የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለህዝብ የጤና ጠንቅ የሚያመጡ ጎጂ ነገሮችና፣ ሽቀጦች ጥቅም ላይ እዳይውሉ እንዳይሸጡና እንዳይከፋፈሉ ያደርጋል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲወገዱ ያደርጋል።
9. የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ከወረዳው ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በዚሁ ዙሪያ የሚካሄድ መንግስታዊና መንግስታ ያልሆኑ አካላት እንቅስቃሴን ያስተባብራል የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
10. የኤች.አይ.ቪ ኤድስን በሚመለከት በህብረተሰቡ የተሟላ ግንዛቤ እንዲፈጠር ከወረዳው ኤች.ቸይ.ቪ ኤድስ ጽ/ቤት ጋር በጋራ ይሰራል።
11. ወቅታዊናመደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት እና ለክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ 15

የትምህርት ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ትምህርት በተመለከተ የሚወጡ ፖሊሲዎች አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎችን በወረዳው ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።
2. በወረዳው ውስጥ የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ይገነባል ያስተዳድራል የውስጥ ቁሳቁስ እንዲሟላቸው ያደርጋል።
3. በወረዳው አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል።
4. መደበኛ ያልሆኑ የጎልማሶች ትምህርት ቢሮና ተፈፃሚ እንዲሆኑ ከክልሉ ትምህርት ቢሮና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል።
5. ለትምህርት ጥራት የተቀመጡ መመዘኛዎች መከበራቸውን የትምህርት ግብዓቶች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መዳረሳቸውን ያረጋግጣል።
6. በወረዳው የሚካሄድን ማሃይምነት የማጥፋት ስራ በበላይነት ይመራል። ይቆጣጠራል ተመሳሳይ አላማ ላላቸው አካላት ተገቢውን ድጋፍና ትብብር ያደርጋል።
7. ህብረተሰቡ የአፋርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያገኝበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል በአፋርኛና ላቲን ጽሁፎች ዙሪያ በወረዳው ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም በጋራ ተባብሮ ይሰራል።
8. በወረዳው ላሉ መምህራን የስልጠና እድል የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል ይህን በተመለከተ ከክልል ትምህርት ቢሮና ከአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር የመምህራን አቅም እንዲገነባ ያደርጋል።
9. በተማሪዎች ላይ የሚያጋጥሙን የትምህርት መድገምና ማቋረጥ በወረዳው የሚታይ ከሆነ ምክንያቱን ያጠናል። ችግሮቹ የሚወገዱበትን ስልት ይቀይሳል ይተገብራል።
10. ትምህርት በየወረዳው እየተስፋፋ እንዲሄድ ከህብረተሰቡና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል የስተባብራል፣
11. በመማር ማስተማር ሂደት ላይ በተደራጀ መልኩ እንቅፋትና ችግር በሚፈጥሩ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ላይ እርምጃ ይወስዳል። ችግሩ ድጋሜ እንዳይከሰት ጥረት ያደርጋል።
12. በወረዳው የሚገኙ ልጃገረዶች በተለይም የአርብቶ አደሩ ልጃገረዶች ትምህርት የሚያገኙበትንና ወደ ት/ቤት የሚመጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ወላጆቻቸውም ጋር የምክክር መድረክ ያፈጥራል።
13. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት እና ለክልሉ ትምህርት ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ 16

የማስታወቂያና ህዝብ አደረጃጀት ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የወረዳው መስተዳድር ቃል አቀባይ በመሆን ይሰራል።
2. በወረዳው የሚሰሩ ስራዎችን በመከታተልና በማስተዋወቅ የወረዳው ህዝብ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያገኝ ያደርጋል።
3. በመንግስት እቅዶችና አፈፃፀም ዙሪያ የአርብቶ አደሩና የከተማው ነዋሪዎች ገንቢ የሆነ ትችትና ማስተካከያ ወይም የመፍትሄ ሃሳብ የሚያቀርቡበትን መድረክ በየጊዜው ያመቻቻል ህብረተሰቡ በዚህ ጉዳይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይረዳል።
4. የክልሉ መንግስት የነደፋቸውን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች ፕሮግራሞች እና አሠራሮች እንዲሁም የፀደቁ አዋጆችና ደንቦች የወረዳው ህዝብ በትክክል እንዲገነዘባቸውና እንዲያውቋቸው በተለያዩ ዘዴዎች የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል።
5. የወረዳውን ባህላዊ እሴቶች ይጠብቃል ይህን በተመለከተ ከክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር ይሰራል።
6. የወረዳው ህዝብ ጉልበቱን ገንዘቡንና እውቀቱን በማስተባበር በወረዳው የልማት ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያነሳሳል ያስተባብራል ያስተምራል።
7. በወረዳው ያሉ ማህበራት ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር የተሞክሮ ልውውጥና መደጋገፍ እንዲያደርጉና በቅንጅት እንዲንቀሳቀሱ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል።
8. በወረዳው ስራ አጥነትንና ሌሎች የማህበራዊ እድገት ጠንቆች ተወግደው ዜጎች አምራች ኃይል እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።
9. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በወረዳው ውስጥ በስራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለሙያው አመዳደብ ጥናት ያደርጋል።
10. አግባብ ካላቸው አከላት ጋር በመተባበር በወረዳው ውስጥ የሚገኙ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል ሲፈቅድም ተግባራዊ ያደርጋል።
11. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብና የህፃናት ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የጋብቻ ስርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን በወረዳው ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።
12. የወረዳው ወጣት የህገ-መንግስት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው ያበረታታል።
13. በክልሉ የሚወጡና ወጣቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና እቅዶች በወረዳው እንዲፈፀሙ ያደርጋል።
14. የወረዳው ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ዴስክን በባይነት ይመራል ይቆጣጠራል ይከታተላል፡

15. የወረዳው ወጣት የክልሉንና የአገሩን ባህል እንዲጠብቅና እንዲያሳድግ ያነሳሳል የወጣቱን አጠቃላይ ስብዕና ለማጠናከር የሚያስችሉ ተግባራት ይፈፅማል።
16. በወረዳው ስፖርት እንዲያድግና እንዲስፋፋ ያደርጋል በወረዳው ለሚቋቋመው የስፖርት ማህበራት እንቅስቃሴ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰታል ያበረታታል።
17. አቅም በሚፈቅድ መጠን በወረዳው የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች እንዲስፋፋ ያደርጋል።
18. የወረዳው ወጣት በልማት ስራዎች እና ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በመከላከል ዙሪያ በማደራጀት ለስራ እንዲነሳሱ ያደርጋል ያስተባብራል ያግዛል።
19. በወረዳ ደረጃ የስፖርት ውድድሮ ያደርጋል የባህልና ስፖርት እንዲታወቅና እንዲያድግ የተለያዩ ስራዎች ይሰራል።
20. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት እና እንዲሰራ ባህሪያቸው ለክልሉ ማስታወቂያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮና ለህዝብ አደረጃጀት ሠ/ማ/ጉ/ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ **17**

የውሃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የውሃ ሃብትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች በወረዳው ተፈፃሚ ስለመሆናቸው ይቆጣጠራል ይከታተላል።
2. በወረዳው የተመጣጠነ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ስርጭት መሰረት ያደረገ እ ቅድ ያወጣል ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ተፈፃሚነቱ በጋራ ይሰራል።
3. በወረዳው ህብረተሰቡን የሚያሳትፉ የመጠጥ ውሃ አስተዳደር ኮሚቴዎች ያቋቁማል። ያስተባብራል ይከታተላል ይቆጣጠራል የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል።
4. የምንጭ ማጎልበትና የውሃ ማቆር ስራዎችን ይሰራል። በዚህ መልኩ የወረዳው አርብቶ አደር ያስተባብራል።
5. ከሚመለከታቸው አካት ጋር በመተባበር በወረዳው ውስጥ በመንግስወት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተሰርተው ወረዳው የተረከባቸውን የመጠጥ ውሃና የመስኖ ተቋማትን ለአርብቶ አደሩና ለከተማው ነዋሪ ዘላቂ አገልግሎት የሚሰጡበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።
6. በወረዳው በመንግስትም ሆነ በመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚሰሩ የመጠጥ ውሃና የመስኖ ስራዎችን ያስተባብራል። ይቆጣጠራል ድጋፍ ይሰጣል።
7. ስራውን በተመለከተ ወቅታዊና መደበኛ ሪፖርቶችን ለወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት እና ለክልሉ ውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ 18

የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የሴቶች ጉዳይ በተመለከተ የወጡ ፖሊሲዎችን እና ህጎችን በወረዳው ተፈፃሚ ያደርጋል። በሌሎች መ/ቤቶች ተፈፃሚ ስለመሆናቸው ይቆጣጠራል ይከታተላል።
2. በወረዳው በሴቶች ጉዳይ ላይ የሚሰሩ አካላት በተደራጀ መልኩ እንዲሰሩ ያደርጋል ያስተባብራል።
3. በወረዳው የሚወጡ የልማት እቅዶች የሴቶች ጉዳይን ማካተቱን ያረጋግጣል አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል።
4. በወረዳው ሴቶች ላይ የመደርሱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል ያስፈፅማል።
5. ሴቶች በተለይም ሴት አርብቶ አደሮች በልማትና በዴሞክራሲ ግንባታ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስተባብራል እንዲደራጁ ያደርጋል።
6. በወረዳው የሚገኙ ልጃገረዶች በተለይም የአርብቶ አደሩ ልጃገረዶች ትምህርት የሚያገኙበትንና ወደ ት/ቤት የሚመጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል። ከወላጆቻቸውንና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ይፈጥራል። ያስተባብራል።
7. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ሴት አርብቶ አደሮችና የከተማ ነዋሪዎች በተለያዩ ሙያዎች የሚሰለጥኑበት የሚደራጁበትና የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን እድል ከክልሉ የሴቶች ጉዳይና አርበቶ አደር ግ/ገ/ል/ቢሮዎች እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እድሉ ሲፈጠር አፈፃፀሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
8. ወቅታዊናመደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳ መስተዳድር ም/ቤት እና ለክልሉ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ያቀርባል።

አንቀጽ 19

የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ በዋጅ ቁጥር 13/94 አንቀጽ 21 ለወረዳ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. በወረዳው ውስጥ በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎችን እቅዶን ያወጣል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል።
2. የወረዳው ነዋሪ ህዝብ በተለይም አርብቶ አደሩ ስለ ኤች አይ.ቪ ኤድስና ስለጉዳቱ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ የተለያዩ መድረኮችን ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል።

3. በስሩ የሚገኙ ቀበሌዎች ፀረኤች አይ.ቪ ኤድስ ክበባት እንቅስቃሴን በቅርብ ይከታተላል።
4. ጋብቻ ለመፈፀም አቅማቸው ለደረሰ የአርብቶ አደሩና የከተማ ነዋሪዎች ስለ ኤች አይ.ቪ ኤድስና ስለ ጎጂ ልማዶች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ምርመራ የማድረተግ ባህል እንዲዳብር ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተለያዩ መንገድ ያስተምራል ያሳውቃል።
5. የወራው ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ገፅታ መረጃዎችን ያስባስባል ያጠናቅራል እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ክልሎች ሪፖርት ያደርጋል።
6. በወረዳው የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎ ላይ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት እንቅስቃሴን ያስተባብራል የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
7. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳው መስተዳድር ም/ቤትና ለዞኑ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ያቀርባል።

አንቀጽ 20

የፍትህ ጽ/ቤት

ጽ/ቤቱ የሚከተለው ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወረዳው አስፈፃሚ አካላት የህግ አማካሪ ሆኖ ያገለግላል።
2. የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣን በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ይከራከራል።
3. በወረዳው ለሚገኙ አስፈፃሚ አካላት ጽ/ቤቶች የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣን በሆኑ በፍታ ብሔር ጉዳይ ላይ ሲከሰሱም ሆነ ሲከሰሱ ወረዳው ን ወክሎ ይከራከራል።
4. በወረዳው ወንል ተፈ ፅሚ ብሎ ሰያምን ምርመራ እንዲካሄድ ያዛል።
5. በወረዳው ውስጥ ሁሉም መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ማህበራትና ግለሰቦች ዘንድ ህጎች መከራቸውን ያረጋግጣል።
6. የወረዳው ህዝብ የህግ ግንዛቤ እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ያስተምራል።
7. ከክልሉ ፍትህቢሮ ተለይቶ የሚሰጠውን መመሪያ መሠረት በማድረግ በወረዳው የውልና የማስረጃ ምዝገባዎችን ያካሂዳል።
8. በወረዳው በእስር ላይ የሚገኙ ግለሰቦችን የታሰሩበትን ምክንያት ህጋዊነት ይከታተላል። ሰብዓዊ መብታቸውን መከበሩን ያረጋግጣል።

9. ወቅታዊና መደበኛ የጽ/ቤቱን የስራ ሪፖርቶች ለወረዳው አስተዳዳሪ እና ለዞኑ ፍትህ መምሪያ ያቀርባል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 21

የወረዳ አስፈፃሚ ጽ/ቤቶ ከክልል ቢሮዎች ጋር ስላላቸው የስራ ግንኙነት

1. የክልሉ አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ስ/ተግ/ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 30/98 ›"ቀጽ 11/5/ ድንጋጌ መሠረት፦

G/ ¾¡MM u=a‹ u¨[Ç KT>Ñ–< ê/u?„‹ U‡ ¾›c^` e`¯ƒ እንዲኖራቸው በሰው ኃይል አቅማቸው የሚያድግበትን ሁኔታ ይፈጥራሉ።

K/ ¾¨[Ç አስፈፃሚ ጽ/ቤቶች በክልል ለሚገኙ ቢሮዎች እንደ የሥራ ባህሪቸው የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በወቅቱ ይልካሉ ቢሮዎቹም ይህንኑ ይከታተላሉ ስለስራው አጠቃላይ ሁኔታ ክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሪፖርት ያደርጋሉ።

ሐ/ አስፈላጊ ሆኑ ሲገኝ የወረዳ ጽ/ቤቶች የክልል ቢሮዎችን የቴክኒክ ድጋፍ ይጠይቃሉ ቢሮዎቹም አቅም የፈቀደውን የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋሉ።

2. ለወራ አስፈፃሚ አካላት ጽ/ቤቶች በግልፅ ያልተሰጡ ስራዎች የክልል ቢሮዎች ስራ ይሆናል።

አንቀጽ 22

ስለ ሌሎች ካቢኔ ያልሆኑ የወረዳ ፅ/ቤቶች መቋቋምና ተጠሪነት

1. የወረዳ ፍትህ.ፖሊስና፣ ሚሊሽያ የካቢኔ አባል ሳይሆኑ በዚህ አዋጅ በጽ/ቤት ደረጃ ተቋቁመዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተዘረዘሩት የፖሊስና ሚሊሻ ጽ/ቤቶች ስልጣንና ተግባራቸው ለክልል እናት መ/ቤቶቻቸው የተሰጠው ስልጣንና ተግባር ሆኖ በወረዳ ደረጃ ይጠቀሙበታል።
3. የፖሊስና የሚሊሽያ ጽ/ቤቶች ተጠሪነታቸው ለወረዳው የፀጥታና አስተዳደር ጉዳዮችና ለዞኑ መምሪያዎቻቸው ይሆናል።
4. የፍትህ ጽ/ቤት እና የወረዳው የገጠር መንገድ ዴስክ ተጠሪነት ለወረዳው አስተዳዳሪ ይሆናል።

አንቀጽ 23

ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች

ይህ አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግና ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

አንቀጽ 24

ደንብ የማውጣት ስልጣን

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል።

አንቀጽ 25

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ሰኔ---------- ቀን 1998 ዓ.ም

እስማኤል አለ. ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር